# አምላክ ለእኛ ብሎ

አምላክ ለእኛ ብሎ ቢያፈሰው ደሙን፣
ለምን ከለከለች ፀሐይ ብርሃኗን፣
የከበረው ሥጋ የከበረው ደም፣
በመስቀል ላይ ዋለ በኢየሩሳሌም።

እዩት ኢየሱስን መስቀሉ ማማሩ፣
ለተመራመረው ብዙ ነው ምሥጢሩ።

ቢመቱት ቢሰቅሉት ቢያላግጡበት፣
ምንም አላገኙም ከርሱ ዘንድ ስህተት፣
ፈጣሪ መሆኑን ምሥጢሩ ገብቷት፣
ጌታን አልይዝ አለች ግዑዟ መሬት።

እዩት ኢየሱስን ...

ይህ ትልቅ ንጉሥ ሲገለጥ በሰማይ፣
የናቁት የወጉት ይሉለታል ዋይ ዋይ፣
ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሲሸሹ፣
ወዴት ልግባ ይላል ትልቁ ትንሹ።

እዩት ኢየሱስን ...

ወደ ሰማይ ያረገው የከበረው ሥጋ፣
ዳግመኛ መምጣቱን ሁላችን አንዘንጋ፣
በሰማይ ለሚኖር ቅዱስ አባታችን፣
ምስጋና ይድረሰው ከእኛ ከሁላችን።

እዩት ኢየሱስን ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org